# ተቅዋ

ገና ከጅምሩ ሁሉም ሰው ያወቀው
የተቀበሉት ፍጥረታት ሁሉ አምነው
የስልጣኔ ምንጭ የ እውቀት መጀመሪያው
የጥበባት ሁሉ አልፋና ኦሜጋው
ሌላ ምንም አይደል አላህን መፍራት ነው

አፍንም ሲከፍቱ ደፍሮ ሊያስተምሩ
መንገድ እንዳይስቱ ወጥተው ከመስመሩ
ካጥፊዎቹ ወገን እንዳይደመሩ
ማተኮር መልካም ነው ወደ ቁም ነገሩ
ወስዋስ እንዳትገቡ ጌታችሁን ፍሩ

አላህን የፈራ አይችልም ሊሳሳት
አትደፍርም ምላሱ ወንድሙን ለማማት
ልብም አትከጅልም ልታብጥ በኩራት
ልትነሳ ቆርጣ ወገኗን ለማጥፋት
አይደፍራትም ከቶ ተንኮልና ቅናት
ባለቤት ናትና የእውቀት ሁሉ እናት
የታደለች መንፈስ ጌታዋን በመፍራት

የተቅዋን ጣፋጭ ማር የቀመሰች ነፍስ
ሊቀርባት አይችልም የሸይጣን ወስዋስ
ማንም አያግዳት ኋላ ከመድረስ
ቀልቧ ወደተመኘው ጀነቱል ፊርደውስ

የተቅዋን ውብ ካባ የለበሰች ገላ
ከቶ አይቻላትም ሃራምን ልትበላ
መቅደሷም እሺ አይል አይሰጥም ከለላ
ሊገነባ ዘንጉን ባአላህ በተጠላ

የተቅዋን ምርጥ ሽታ ያሸተተ አፍንጫ
ፍጹም አልቆለታል አይኖረውም ምርጫ
ቀዳዳው ተደፍኗል የለውም በር መውጫ
ወደ ኩፍር መንገድ መሰላል መርገጫ

የተቅዋን ክብር ዝና ያዳመጠ ጆሮ
ቦታ አይኖረውም ለሸይጣን እሮሮ
ምን ቢጥር ቢሞክር ቢያሰማ እንጉርጉሮ
ጠዋት ማታ ቢላዝን ቲቪና ራዲዮ

የተቅዋን ሥስ ገላ አገላብጦ ዳሶ
ከቶ አይሆንለትም አይነካም ጨርሶ
ሃላል ያልሆነውን ያአላህን ቃል ጥሶ
የሙስተቂሙን ሲራጥ በሃራም አፍርሶ

የተቅዋን ቁንጅና አይቶና አድንቆ
እንዴት ይቻላዋል እግር ሊሄድ ርቆ
ቀናውን ጎዳና ችላ ብሎ ንቆ
የተከበረውን የአላህን ቤት ለቆ

የተቅዋን ጎዳና የረገጠች እግር
አትከጅልም ከቶ ልትሄድ ወደ ከምር
ለሃራምነቱ የሌለለት ወደር
የጥፋቶች እናት በሰማይ በምድር

ተቅዋ የሌለው ሰው አይበጅም ለራሱ
ውሸትን አትፈራም ቀጣፊ ምላሱ
አፍንጫው ከማሽተት አይኖቹም ከማየት
ድንበር እየጣሱ
ሰኪና አይኖራትም ይጨንቃታል ነፍሱ

ያላህን ፍራቻ ያልተገነዘበ
በተቅዋ ግሳፄ መንፈሱ ያላደበ
በዱንያ ፍቅር አዕምሮው የደደበ
አይሆንም ለማንም ነፍሱን ተውባ ካልመገበ

የዚህች ምድር ህይወት አይደለም ዘላቂ
መሆን የማይቀር ነው ኋላ ተጠያቂ
በሆነው አልሃኪም ሁሉንም አዋቂ